Career READINESS

Get an Early Edge on YOUR FUTURE

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

# ለኮሌጅ አማራጮች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሞንትጎመሪ ኮሌጅ (MC) በአጋርነት ለኮሌጅ ዝግጁ ለሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሁለቱም በ MCPS እና በሞንትጎመሪ ኮሌጅ መመዝገብ የሚያስችላቸዉን የተለያዩ የመንታ/የሁለትዮሽ የምዝገባ ዕድሎችን ይሰጣሉ።

የመንታ/የሁለትዮሽ ምዝገባ ተማሪዎች ለስቴታቸዉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ በተሳካ ሁኔታ ለተጠናቀቁ የኮሌጅ ኮርሶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክሬዲት በማግኘት ላይ ሳሉ፣ ጊዜ እና ገንዘባቸዉን በመቆጠብ የአሶሺዬት እና/ወይም የባችለር ዲግሪያቸዉን ለማግኘት ያስችላቸዋል።

ተማሪዎች የ MC ኮርሶችን በድረ-ገጽ ላይ፣ በኮሌጅ ካምፓሶች እና በተመረጡ የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመውሰድ ይችላሉ። ተማሪዎች የትምህርት እና የስራ ግቦቻቸውን ለማሳካት የሚያስችሏቸው የተለያዩ አማራጮች እንዳሏቸው ለማረጋገጥ MCPS እና MC በመተባበር ይሰራሉ።



#CareerReady

## ቀዳሚ ኮሌጅ

ተማሪዎች 11ኛ እና 12ኛ ክፍል እያሉ በሞንትጎመሪ ኮሌጅ በጀርመንታውን፣ በሮክቪል ወይም በታኮማ ፓርክ/ሲልቨር ስፕሪንግ ሁሉንም የኮሌጅ ኮርሶች ይወስዳሉ። ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ እና በአሶሽዬት ዲግሪ ይመረቃሉ። ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል ያመለክቱና በሚመርጡት የዲግሪ ፕሮግራም መሰረት የሚፈለጉ የኮሌጅ መስፈርቶችን (ለምሳሌ፦ GPA፣ የግምገማ ውጤቶች፣ የኮርሶች ዉጤቶች፣ ወዘተ) ማሟላት አለባቸው። አሥራ አንድ የዲግሪ አማራጮች ይሰጣሉ። ለሚያስፈልጉ ኮርሶች የመማሪያ መጽሀፍትና የትምህርት ወጪ ይሸፈናል። ለፋይናንሻል ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የኮሌጅ የትምህርት ወጪ ይሸፈናል።

## ወደ አውታረ-መረብ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የሚያመሩ መንገዶች

ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በኮሌጅ ኮርሶች ጥምረት፣ የ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ፣ የአውታረመረብ ኢንፎርሜሽን ኢንዱስትሪ ማረጋገጫ እና የአፕላይድ ሳይንስ አሶሽየት ዲግሪ ያገኛሉ። ተማሪዎች የስድስት ሳምንት ኢንተርንሺፕ የሚያጠናቅቁ ሲሆን የኢንዱስትሪ አሰልጣኞች ደግሞ ግስጋሴያቸዉን ይደግፋሉ። ይህ ፕሮግራም በክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጥ ሲሆን የአካባቢ ት/ቤታቸው ክላርክስበርግ ለሆነ፣ እንዲሁም ፍላጎት ላላቸው ለደማስከስ፣ ሰኔካቫሊ፣ እና ዋትኪንስ ተማሪዎች በሎተሪ ዕጣ አማካይነት ክፍት ነው። ተማሪዎች ከ8ኛ ክፍል ያመለክታሉ። ለሚያስፈልጉ ኮርሶች የመማሪያ መጻሕፍት፣ የትምህርት እና የኮሌጅ ወጪዎች ይሸፈናሉ።

## ሞንትጎመሪ ኮሌጅ መካከለኛ ኮሌጅ (MC)

ተማሪዎች በ AP ኮርሶች እና በተጓዳኝ የፈተና ውጤቶች፣ የኮሌጅ-ደረጃ ፈተና ፕሮግራም ፈተናዎች፣ እና/ወይም በ MC ኮርሶች አማካይነት የኮሌጅ ነጥቦችን ያገኛሉ። ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ካምፓስ ዉስጥ እያሉ ወደ ኮሌጅ ካምፓስ የኮርስ ስራዎች፣ ከተለምዷዊዉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተሞክሮ ወደ ኮሌጅ መሰል ተሞክሮ በሂደት ሽግግር አማካይነት ይደገፋሉ። ይህ ፕሮግራም በኖርዝ ዌስት እና በኖርዝዉድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይሰጣል። የኖርዝ ዌስት ፕሮግራም በአጠቃላይ ምህንድስና እና በአጠቃላይ ጥናት ድግሪ ከMC የሚያቀርብ ሲሆን የአካባቢ ት/ቤታቸው ኖርዝ ዌስት ለሆነ፣ እንዲሁም ፍላጎት ላላቸው ለክላርክስበርግ፣ ደማስከስ፣ጌትስበርግ፣ ማግሩደር፣ ፑልስቪል፣ኩዊንስ ኦርቻርድ፣ሴኔካቫሊ እና ለዋትኪንስ ተማሪዎች በዕጣ ክፍት ነው። የኖርዝዉድ ፕሮግራም በአጠቃላይ ጥናት ድግሪ ከ MC የሚያቀርብ ሲሆን የአካባቢ ት/ቤታቸው ኖርዝዉድ ለሆነ፣እንዲሁም ፍላጎት ላላቸው ቤተዝዳ-ቼቪ ቼዝ (Bethesda-Chevy Chase)፣ ቸርቺል (Churchill)፣ ዳወንካውንቲ ኮንሰርሽየም (Downcounty Consortium)፣ ኖርዝኢስት ኮንሰርሽየም (Northeast Consortium)፣ ዋልተር ጆንሰን (Walter Johnson)፣ ሪቻርድ ሞንትጎመሪ (Richard Montgomery)፣ ሮክቪል (Rockville)፣ ሼርውድ (Sherwood)፣ ዋልት ዊትማን (Walt Whitman)፣ እና ለዉቶን (Wootton) ተማሪዎች በሎተሪ ዕጣ አማካይነት ክፍት ነው። ተማሪዎች ከ 8ኛ ክፍል ያመለክታሉ። ለፋይናንሻል ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የመጀመሪያዎቹ አራት ኮርሶች ክፍያ ነፃ ነው። ለተጨማሪ ኮርሶች የትምህርት ክፍያ ወጪ ለሶስት-ክሬዲት ኮርስ በግምት $355 * ነው። ለ MC ሁለተኛ ደረጃ ግራንት/ዕርዳታ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የኮሌጅ ክፍያዎች፣ እና ተጨማሪ ከኮርስ ጋር ተዛማጅነት ያለው ወጪ ሙሉ በሙሉ ሊሸፈን ይችላል። ተማሪዎች ለመማሪያ መጻሕፍት መክፈል አለባቸዉ።

## የኮሌጅ ጅማሮ ድጋፍ/Jump Start to College

Jump Start ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማቸዉን ለማግኘት በሚሰሩበት ወቅት በተቻለ መጠን ብዙ የኮሌጅ ኮርሶችን እንዲያጠናቅቁ ለመርዳት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ አማራጭ ለሁሉም የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አለ። ለፋይናንሻል ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የመጀመሪያዎቹ አራት ኮርሶች ክፍያ ነፃ ነው። ለተጨማሪ ኮርሶች የትምህርት ክፍያ ወጪ ለሶስት-ክሬዲት ኮርስ በግምት $355 * ነው። ለ MC ሁለተኛ ደረጃ ግራንት/ዕርዳታ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የኮሌጅ ክፍያዎች፣ እና ተጨማሪ ከኮርስ ጋር ተዛማጅነት ያለው ወጪ ሙሉ በሙሉ ሊሸፈን ይችላል። ተማሪዎች ለመማሪያ መጻሕፍት መክፈል አለባቸዉ።

*የትምህርት ኮርስ ክፍያ፣ የኮሌጅ ክፍያዎች (ለምሳሌ፣ የመገልገያ ክፍያ፣ የቴክኖሎጂ ክፍያ) እና የመማሪያ መጻሕፍት በ MC የሚወሰኑ እና በኮርስ፣በክፍል፣ እና በፕሮፌሰርም ይለያያሉ። በየዓመቱ ሊለያይ የሚችለዉ የወላጆች ትክክለኛዉ ወጪ በ MC ይጋራል። ከላይ የተጠቀሱት ወጭዎች የ 2019 ን መረጃ መሠረት ያደረጉ አማካይ ወጭዎች ናቸው።

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፡-** የመንታ/የሁለትዮሽ ምዝገባ እድሎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪዎን፣ የመንታ/የሁለትዮሽ ምዝገባ ፕሮግራም ረዳት ያነጋግሩ፣ ወይም ይህን QR code ስካን ያድርጉ፡-

- https://montgomeryschoolsmd.org/curriculum/partnerships/dual-enrollment.aspx